በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# ጠላትና የጦር ዕቃ

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ኅዳር ፯ ቀን ፳፻፬ ዓ.ም.

# <u>ጠላትና የጦር ዕቃ</u>

*መግቢያ*

- ድል አድራጊነት ከመንፈሳዊና ሥነ ልቦናዊ አመለካከት አንጻር ከሰይጣን ጋር በምናደርገው መንፈሳዊ ውጊያ አበረታች ኃይል ነው፡፡
- በተሸናፊነትና በደካማነት ስሜት ወደ ጦርነት መሄድ ውጤቱ ተሸናፊነት ነው፡፡ በአንጻሩ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ተመክተን ወደ ጦርነት መግባት ውጤቱ ድል አድራጊነት ነው፡፡ ‹‹በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ፡፡›› <u>*ኤፌ 6፡10፡፡*</u>
- ያለረዳት ብቻንን መሆናችንን ስንረዳ የሚያስፈልገንን ኃይልና ብርታትን ብቻውን ሊሰጠን ወደ ሚችል እግዚአብሔር መሄድ ይጠበቅብናል፡፡
- ልበ አምላክ ዳዊ ከሳኦል ጋር በነበረው ጦርነት ያደረገው ይህንኑ ነው፡፡ በዚህም በጦርነቱ አሸናፊ በመሆን ለሕዝቡ ሰላምና ደስታው ወደ ልቦናው እንዲመለስ ማድረግ ችሎ ነበር፡፡
- ስለዚህ እያንዳንዱን ዕለት እግዚአብሔር ኃይሉንና ብርታቱን እንዲሰጠን ሳንጠይቅ ከመጀመር እንቆጠብ፡፡

*ጠላታችን ማነው*

- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዲያቢሎስ መኖር፣ ስለተፈጥሮው፣ በእኛም ላይ ሳያቋርጥ ስለሚሠራው ክፉ ሥራ በሚያስረዱ ብዙ ማስረጃዎች የተሞላ ነው፡፡

# ጠላትና የጦር ዕቃ

## *ጠላታችን ማነው*

- ‹‹መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።›› ***ኤፌ 6፡12።***
- ‹‹በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና፤ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።›› ***ቀዳ ጴጥ 5፡8-9።***
- ‹‹በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ አንስተውምና።›› ***ካል ቆሮ 2፡11።***
- ‹‹ፈቃዱን ለማድረግ በዲያብሎስ ሕያዋን ሆነው ከተያዙበት ወጥመድ ወጥተው፥ ወደ አእምሮ ይመለሳሉ ብሎ የሚቃወሙትን በየዋህነት ይቅጣ።›› ***ካል ጢሞ 2፡26።***
- ‹‹ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።›› ***ራእ 2፡10።***
- ‹‹የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።›› ***ማቴ 13፡19።***
- ‹‹ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም።›› ***ዮሐ 17፡15።***
- ‹‹ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው።›› ***ካል ተሰ 3፡3።***

# ጠላትና የጦር ዕቃ

## *ሰማያውያን ሆነው ክፋትን የሚያደርጉና የሚያስደርጉ*

- የወደቁት መላዕክት በእግዚአብሔር ላይ የምናምጽበትን በደለኛነትን በውስጣችን በመትከል በሥጋ ፍላጎት በመጣል ይዋጉናል፡፡
- ይህም በበለዓም ሕይወት ታውቋል፡፡ እግዚአብሔር የባረካቸውን ሕዝቦች እንዳይረግም ቢነገረውም እስራኤላውያን በገዛ እጃቸው የሚወድቁበትን ምክር በመምከር በአሕዛብ ሴቶች እጅ ጥሎአቸዋል፡፡ *ዘኍ 22-25፡፡*

## *የጠላት ጦር*

- የጠላትን ጦር አስመልክቶ ቅዱስ ጳውሎስ ፍላጻ ብሎ ጽፎልናል፡፡ አንዴ ሲለኮስ በወደቀበት ቦታ ያገኘውን ሁሉ የማቃጠል ኃይል አለው፡፡ ሰይጣንና መላዕክቱ ሁሉ በኃጢአት በሚመራው በዚህ ዓለም ይህን ፍላፃ በየጊዜው ይወረውራሉ፡፡

## *ድል ለማን ነው?*

- መጽሐፍ ቅዱስ ድል ማድረግ ለጌታችን ለአምላካችን ለኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በመግለጽ ቃል ገብቶልናል፡፡
- ‹‹በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን፡፡›› ***ሮሜ 8፡37፡፡***
- ‹‹እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም፡፡›› ***ራእ 12፡11፡፡***

# ጠላትና የጦር ዕቃ

***ድል ለማን ነው?***

- ‹‹አባቶች ሆይ፥ ከመጀመሪያ የነበረውን አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ። ጐበዞች ሆይ፥ ብርቱዎች ስለ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስለ አሸነፋችሁ እጽፍላችኋለሁ።›› ***<u>ቀዳ ዮሐ 2፡14፡፡</u>***
- <<ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።›› ***<u>ቀዳ ቆሮ 15፡57፡፡</u>***
- <<ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን፡፡›› ***<u>ካል ቆሮ 2፡14፡፡</u>***
- <<የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።›› ***<u>ሮሜ 16፡20፡፡</u>***
- የጦር ዕቃችን
- <<የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።›› ***<u>ኤፌ 6፡11</u>*** እንደተባለው ከስድስት የተለያዩ አካላት ቢሠራም አንድ የጦር ዕቃ ሆኖ ስድስቱም አካላት ግን ሁልጊዜ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡
- የጦር ዕቃው ቁሳዊ ቢመስልም ሙሉ ለሙሉ መንፈሳዊውን ነገር የሚመለከት ሆኖ ድል ከሚያደርግ ከእግዚአብሔር የተሰጠን የምንለብሰው የጦር ዕቃ ልብስ ነው፡፡ እያንዳንዳቸውን እንደሚከተለው እንመልከታቸው፡፡

# ጠላትና የጦር ዕቃ

## *1. የእውነት ትጥቅ*

- ‹‹እንግዲህ ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ፥ ቁሙ።›› ***ኤፌ 6፡14፡፡***
- ይህ የመጀመሪያው ትጥቅ ሆኖ በወገብ የምንታጠቀው ነው፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ ‹‹ስለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተስፋ አድርጉ፡፡›› ***ቀዳ ጴጥ 1፡13፡፡*** እንዳለ ይህ ትጥቅ ከአእምሮ፣ ከልብና ከስሜቶቻችን የሚወጣ ወደነርሱም የሚገባ የፈቃደኝነት ሥራ ነው፡፡ በዚህ ክፍል የተጠቀሰውም እውነት አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡
    - ‹‹ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው። እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።›› ***ዮሐ 8፡31-32፡36፡፡***
    - ‹‹ኢየሱስም፦ እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።›› ***ዮሐ 14፡6፡፡***
    - ‹‹አብ ወልድን ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል።›› ***ቀዳ ዮሐ 5፡20፡፡***
- በንቃት ሆነን እውነተኛ የሆነውን የእምነታችንን አስተምህሮ በመከተል በአእምሮአችን እንዲቀረጽ፣ በልቦናችን እንዲያድርና ስሜቶቻችን የሚገዙለት መሠረታዊ ለውጥ በሕይወታችን እንዲያመጣ ማድረግ ይገባናል፡፡
    - ‹‹ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ስፋቱና ርዝመቱ ከፍታውም ጥልቅነቱም ምን ያህል መሆኑን ለማስተዋል፥ ከመታወቅም የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር ለማወቅ ትበረቱ ዘንድ፥ እስከ እግዚአብሔርም ፍጹም ሙላት ደርሳችሁ ትሞሉ ዘንድ።›› ***ኤፌ 3፡18-19፡፡***
    - ‹‹ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ። ›› ***ዳን 12፡3፡፡***

# <u>ጠላትና የጦር ዕቃ</u>

## *2. የጽድቅ ጥሩር*

- ‹‹የጽድቅንም ጥሩር ለብሳችሁ፥ ቁሙ።›› ***<u>ኤፌ 6፡14፡፡</u>*** ቅዱስ ጳውሎስ ስለሁለት ዓይነት ጽድቅ ተናግሯል፡፡
- የመጀመሪያው በእያንዳንዳችን ጥረት ስለሚፈጸም ጽድቅ ሲሆን ይህም ከአዳም የተላለፈብንን ዕዳ በግል ጥረታችን ሊያስወግድልን የማይችል፣ ሕግን እንዳንጥስ ሊጠብቀን የማይችል (በብሉይ የነበሩት ሕግን መፈጸም አልተቻላቸውም)፣ ካሳ አይከፍልም፣ ከሞትም አያድንም ‹‹የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፡፡›› ***<u>ሮሜ 6፡23፡፡</u>***
- ሁለተኛው በጌታችን በአምላካችን ባለን እምነት ያለ ጽድቅ ሲሆን ‹‹አዎን፥ በእውነት ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥ ክርስቶስንም አገኝ ዘንድ፥ በክርስቶስም በማመን ያለው ጽድቅ ማለት በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ጽድቅ እንጂ ከሕግ ለእኔ ያለው ጽድቅ ሳይሆንልኝ፥ በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቈጥራለሁ፡፡›› ***<u>ፊል 3፡9፡፡</u>*** ያለው ነው፡፡ ይህም የቀደመውን በደል የደመሰሰ፣ ሕግን ለመፈጸም የሚያስችለንና ሕግን ከማፍረስ የሚጠብቀን ***<u>ቀዳ ዮሐ 5፡3</u>***፣ ካሣ የተከፈለበት ***<u>ካል ቆሮ 5፡21</u>***፣ እና ከመንፈሳዊ ሞት የምንድንበትና የጽድቅን ሕይወት የምንጎናጸፍበት ነው፡፡ ***<u>ቀዳ ዮሐ 2፡29፡፡</u>***
- ስለዚህ ‹‹ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ።›› ***<u>ራእ 7፡14፡፡</u>*** እንደተባለው እውነትን በመረዳት የጽድቅን እውነተኛ ገጽታ እንድንረዳ የሚያደርገን ሰይጣንም በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ፊት ሊከሰንና ሊረታን እንዳይችል የሚያደርገው በሕይወታችን ቦታም ሆነ ዕድል እንዳይኖረው የሚያደርግ ነው፡፡

# ጠላትና የጦር ዕቃ

### *3. የሰላም ወንጌል*

- ‹‹በሰላም ወንጌልም በመዘጋጀት እግሮቻችሁ ተጫምተው ቁሙ።›› ***ኤፌ 6፡15፡፡***
- የእግዚአብሔርን ጽድቅ በኢየሱስ ክርስቶስ ከፈጸምን ዓለምን የማይሰጠንን ሰላም እናገኛለን፡፡ በጌታችን መወለድ መላዕክት ‹‹ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር›› ***ሉቃ 2፡14*** በማለት ዘምረዋል፡፡ ይህም ሰላም ሦስት ገጽታዎች አሉት፡፡
  - ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር ‹‹ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም። ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።›› ***ዮሐ 14፡27፡፡***
  - ሰላም እርስ በርሳችን ‹‹የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።›› ***ማቴ 5፡9፡፡***
  - ሰላም ከራሳችን ጋር
- መጫሚያው የሚያመለክተው መንቀሳቀስንና በሁለት ደረጃዎች በተግባር ቀድሞ መገኘትን የሚያመለክት ነው፡፡
  1. ከእግዚአብሔርና ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምና ስምምነትን ለማድረግ ዝግጁ መሆን፡፡ ‹‹…›› ***ካል ቆሮ 5፡20፡፡***
  2. የእግዚአብሔርን የምሥራቹን ወንጌል እንደእግዚአብሔር መልዕክተኛ ለዓለም ለማዳረስ ዝግጁ መሆን፡፡ ***ቀዳ ጴጥ 3፡14-15፣ ራእ 12፡11፣ የሐዋ 26፡18፡፡***

# ጠላትና የጦር ዕቃ

***4. የእምነት ጋሻ***

- ‹‹በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፡፡›› ***ኤፌ 6፡16፡፡***
- እምነት በእግዚአብሔር ያለንን ዋስትናና የእርሱንም እውነት መቀበል ነው፡፡ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ያለንን ይኸን እምነት፣ ማደኑንና ይቅርታውንም ለማጥፋት ፍላጻውን ይወረውራል፡፡ እኛም ይኸንን ጠላት የምናሸንፍበት ብቸኛ መንገድ እምነት ነው፡፡
    - ‹‹ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።›› ***ቀዳ ዮሐ 5፡4፡፡***
    - ‹‹በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።›› ***ቀዳ ጴጥ 5፡9፡፡***
    - ‹‹ስለዚህም ምክንያት ይህን መከራ ደግሞ ተቀብዬአለሁ፥ ነገር ግን አላፍርበትም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።›› ***ካል ጢሞ 1፡12፡፡***
    - ‹‹እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።›› ***ቀዳ ዮሐ 4፡16፡፡***
    - ‹‹እግዚአብሔር ቸር፥ ምሕረቱም ለዘላለም፥ እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና።›› ***መዝ 99(100)፡5፡፡***
    - ‹‹የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን ጽፌላችኋለሁ።›› ***ቀዳ ዮሐ 5፡13፡፡***
    - ‹‹እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው።›› ***ሮሜ 10፡17፡፡***
- የእምነት ልብሳችንም በዚህ ዓለም ካለው ፍርሐትና ከጠላት አደጋ ይጠብቀናል፡፡ ‹‹መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ስድብ አውቃለሁ። 210ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመንህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።›› ***ራእ 2፡9-10፡፡***

# ጠላትና የጦር ዕቃ

### 5. የመዳን ራስ ቁር

- <<የመዳንንም ራስ ቁር ያዙ፡፡>> ***ኤፌ 6፡17፣***
- <<እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር>> ***ቀዳ ተሰ 5፡8፣*** <<የተስፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተስፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፡፡>> ***ዕብ 10፡23፣ ቀዳ ተሰ 1፡3፡፡***
- ቁር የተባለው የመዳን ተስፋ ነው፡፡ ከዚህ ዓለም ከተለየን በኋላ ጌታችን በዓይናችን ያለውን እንባ ሁሉ የሚያብስባትን በሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም ያለውን ድል ተስፋ እናደርጋለን፡፡ በዚህም ተስፋ የጌታችን የተስፋ ቃል ኪዳኑን በጽንዓትና በትጋት እንጠባበቃለን ቃል የገባልን የታመነ ነውና፡፡
    - <<ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።>> ***ሮሜ 8፡18፣*** <<የማይታየውን እንጂ የሚታየውን ባንመለከት፥ ቀላል የሆነ የጊዜው መከራችን የክብርን የዘላለም ብዛት ከሁሉ መጠን ይልቅ ያደርግልናልና፤ የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።>> ***ካል ቆሮ 4፡17፣*** <<በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።>> ***ቀዳ ቆሮ 15፡19፣*** <<ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን በመነሣቱ ለሕያው ተስፋና ለማይጠፋ፥ እድፈትም ለሌለበት፥ ለማያልፍም ርስት እንደ ምሕረቱ ብዛት ሁለተኛ የወለደን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ፤ ይህም ርስት በመጨረሻው ዘመን ይገለጥ ዘንድ ለተዘጋጀ መዳን በእምነት በእግዚአብሔር ኃይል ለተጠበቃችሁ ለእናንተ በሰማይ ቀርቶላችኋል።>> ***ቀዳ ጴጥ 1፡5-6፡፡***

# ጠላትና የጦር ዕቃ

### *6. የመንፈስ ሰይፍ*

- ‹‹የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።›› ኤፌ 6፡17፡፡
  - ‹‹የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።›› ***ቆላ 3፡16፡፡***
  - ‹‹አንተ እንዳልበድል፥ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።›› ***መዝ 118(119)፡11፡፡***
  - ‹‹የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፥ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም።›› ***ኢያ 1፡8፣ ማቴ 4፡4፡7፣10፡፡***
- በዚህ ክፍል የምንማረው ከአለቃው ከጌታችን ነው፡፡ የቀረበለትን ፈተና ጠላትን በመቃወም ብቻ ሳይሆን የገዛ ልቦናን መገሰጽ እንዲገባ በመገሰጽም ነው፡፡ በቁጣ ወደክርክር ሳይገባ ለሰይጣን የተቀደሰውን ቃል ጠቅሶ መለሰለት፡፡ በማስተማር ዘመኑም መጀመሪያ ጌታችን የመጻሕፍትን ቃል ‹‹የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ። የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ።›› ሉቃ 4፡17-19 እንደተባለ የሌሎችን ልብ የሚከፍል መሳሪያ አድርጎታል፡፡
- ቅዱስ ጴጥሮስ በመጀመሪያ ስብከቱ ኢዩ 2 እና መዝ 16ን በመጥቀስ አስተምሯል፡፡  እኛም የራሳችንን ሐሳብ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም የሌሎችን ልብ ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ይቻለን ዘንድ ማጥናትና መጥቀስ ያስፈልገናል፡፡

# ጠላትና የጦር ዕቃ

## *7. ጸሎት*

- ‹‹በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤ ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፡፡›› ***ኤፌ 6፡18-19፡፡***
- ስድስቱን የጦር ዕቃዎች ይዘን ያለእግዚአብሔር ወደ ጦርነት ብንወጣ ተሸናፊ መሆናችን እርግጥ ነው፡፡
- በጦርነት መካከል ማንቀላፋት ጠላት በጦርነት መካከል የጦር ዕቃችንን እንዲሰርቅ እናደርገዋለን፡፡
- ንቃት በሌላ በኩል ጽንዓትና ትዕግሥትን ይሻል፡፡ ‹‹እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።›› ***ማቴ 10፡22፡፡***
  - ***ሮሜ 8፡26-27፣ ቀዳ ዮሐ 5፡14፣ ሉቃ 18፡1፤7፤*** ‹‹ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል። እንግዲህ እንደ ባለ አእምሮ አስቡ፡፡›› ***ቀዳ ጴጥ 4፡7፡፡*** ‹‹እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።›› ***ያዕ 5፡16፣ ሉቃ 22፡32፣ ኤፌ 6፡19፣ ዮሐ 14፡12-14***
- ለማጠቃለል ውጊያችን ከሥጋና ከደም ከሰው ጋር ሳይሆን ከሰይጣንና ከርሱ ጋር አብረው ከወደቁ ኃይላት ጋር ነው፡፡
- ነገር ግን ወደጦርነቱ በመንፈስና በሥነ ልቦናችን ታጥቀን ከገባን አሸናፊነቱ የእኛ ነው፡፡ ስድስቱም የጦር ዕቃዎች አብረው የሚሠሩ ሲሆኑ እርስ በርስም የሚደጋገፉ ናቸው፡፡
- ጸሎትም የጦር ዕቃዎቹን የተሳሉና ለአገልግሎትም ብቁ እንዲሆኑ የሚያበቁ ናቸው፡፡ የጌታችን ደሙም የድሉ ምንጭ ነው፡፡

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org